# <u>ሳይከካ ተቦካ--ወይ ባራክ ኦባማ!</u>

ይብላኝ ለአሜሪካ እንጂ ወተት ያው በገሌ ሳልነው ምንም አዲስ ነገር የለውም:: ኦባማ ለውጥ ሲል ቆይቶ ያው እጅ እጅ ያለውን የክሊንተኖችን ፖለቲካ ይዞብን ብቅ ሊል ተዘጋጅቷል:: ወይዘሮ ሂላሪ ክሊንተን የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትሆናለች መባሉና ሂላሪም ከተሰጠኝ ቦታውን እወስዳለሁ ማለቷ አሳሳቢ መሆኑ አልቀረም::

የነገሮችን ውል ለመረዳት አንዱ መንገዱ ጠላት ምን ይላል የሚለው መመዘኛ ነው:: ጠላትን የ ሚያቃጥለውና የሚያናድደው እኛን ሊያስደስተን ይጠበቃልና ነው:: ጠላት ጮቤ ከረገጠ ደግሞ ጉድ ፈላ ማለቱ ትክክል ይሆናል:: የሂላሪ ክሊንተን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርነት የመሾም ሁኔታ ወያኔን አስፈንድቆታል:: የወያኔ ድረ ገፀ የሆነው አይጋ ፎረም ለምሳሌ የደስታ ግጥም ሁሉ አትሞ ሂላሪ መጣች፤ተቃዋሚዎች ከሰሩ ብሎናል:: ወያኔ ለምን ይደሰታል? በመጀመሪያ ኦባማ ስለተመረጠ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖለቲካ ኢትዮጵያን በተመለከተ ይቀየራል ብለው ያሰቡ ካሉ ከእንቅልፋቸው መንቃት አለባቸው ማለት አለብን:: ከዚያ ቀጥሎ ወይዘሮ ክሊንተን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሆኑ መለስ ዜናዊም ሆኑ ሌሎች የቅርብና የሩቅ አምባገነኖች የሚፈሩት ጉዳይ ጭራሽ ሊኖር ባለመቻሉ ነው:: ወይዘሮ ክሊንተን የራሳቸው ጣጣ ያላቸው ቢሆንም እስቲ በባላ ቸው እንጀምር:: በአሜሪካ ያሉ ኢትዮጵያውያን በገንዘብ ሳይቀር የደገፉት ክሊንተን በስልጣን ሳለ ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪካ ሕዝብ ደህንነት ሊቆም ቀርቶ መለስና ኢሳያስን፤ የርዋንዳውን ፖል ካጋሜና የዩጋንዳውን ዮወሪ ሙሴቬኒን አዲስ ዓይነት ዴሞክራቶች ና መሪዎች ብሎ በማሞ ገስ ሲደግፋቸው ቆይቷል:: የአቶ ክሊንተን አማካሪ በአፍሪካ ጉዳይ ላይ የታወቀችው ጌይል ስሚዘ ነበረች:: ጌይል ስሚዝ ደግሞ በሱዳን በነበሩ ስደተኞች ወይዘሪት ግደይ ትባል የነበረች የመለስ ዜናዊና የኢሰያያስ አፈወርቂ የቅርብ ወዳጅና ረዳት የነበረች ናት:: ተቃዋሚውን ሁሉ በአማራ ትምክህተኛነትና በደርግነት ፈርጃ ትወግር የነበረች የፖል ሄንዚ ቀሚስ ለባሽ መንታ:: ወይዘሮ ክሊነትንም ባላቸው በስልጣን ሳሉ ልጃቸውን ይዘው ወደ አስመራ በረው ከኢሳያስና ከሚስቱ ጋር ሸማ ለብሰው በአስመራ እስክስ ያሉት ሳይበቃ የአስመራውን አምባገነን ዴሞክራሲ ያዊ ብለው ያወደሱ ነበሩ:: እስክስ ካሉበተ. ቦታ ትንሽ ራቅ ብሎ በሰንበልና ሌሎች እስር ቤቶች የአቶ ኢሳያስ ተቃዋሚ ተብለው ስንቶቹ በግፍ እየተሰቃዩ እንደነበሩ ለወይዘሮ ክሊንተን እምብዛ ም አላሳሰባቸውም::

ወይዘሮ ክሊንተን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሆኑ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ተሻሽሎ ለመለ ስ ዓይነቶች አምባገነኖች አሳሳቢ የሚሆንበት ሁኔታ የለም:: ለውጥ ለውጥ ብሎ ለስልጣን የበቃ ው ኦባማ እያደር ያው ካወቅነው ከለመድነው አንድ ወይም ተመሳሳይ ሆኖ መቅረቡ የማይቀር ነው:: ሽብርተኝነትን መዋጋት ዋና ስራዬ ነው ማለቱ እንደ መለስ ዓይነት ሎሌዎችን መፈለግን የግድ ያደርግበታል:: የመለስ ጦር በሶማሊያ ሽንፈቱን እየተከናነበ መሆኑና የሶማሊያም ችግርና ቀውስ መባባሱም በዚህ መስክ አያ ኦባማ ከመ ቡሽ መለስን " ሀሎ ሰውየው በርታ እንጂ " ማለቱ መጠበቅ አለበት:: ወይዘሮ ክሊንተን ደግሞ ወዲ አፈወርቂን ዴሞክራሲያዊ መሪ ካሉ

መለስን ማቀፉ አይገዳቸውም፡፡ ምናልባትም እነ ጌይል ስሚዝንም ቦታ ዳግም ይሰጡም ይሆናል ብሎ መጠበቁ አይከፋም፡፡ ይህ ሁሉ ያው መቸም በጉዳዩ ሀ ና ለ እንበል በሚል እንጂ ቡሽ ሄደ ኦባማ መጣ ራይስ ሄደች ክሊንተን መጣች በመሰረቱ ለሀገራችን ነፃነትና ከወያኔ መላቀቅ ሚዛኑ ከፍተኛ አይደለም፡፡ ዋናው ሚዛን ደፊው ጉዳይ የራሳችንን የሕዝባችንን ትግል ማፋፋምና የአሜ ሪካንን ጆሮ ማቅላት/ማግኘት የሚሉ ካሉ ይሁንላቸው/ ነው፡፡ ዲፕሎማሲ ቦታ ያለው ቢሆንም መቸም ቢሆን መቼ ትግልን ሊቀድም አይገባውም፡፡ ስለዚህም እናንት በባዕድ ያላችሁ የሀገሬ ልጆች--ኦባማና ክሊንተንን መማፀኑን ትታቸሁ ወያኔን የሚታገሉትን መርዳቱ ላይ አተኩሩ፡፡

ተካልኝ ዘጉለሌ